**ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ**
**ኢየሱስ ክርስቶስ**
**ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ**
**ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ**

**The Triumphant Lion of the Tribe of Judah**
**Jesus Christ**
**Eternal Priest in the Order of Melche-Zedeq the Ethiopian**
**King of Zion and King of Kings of Ethiopia**

**ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር**
**ድንግል ማርያም**
**እሙ ለአምላክነ፥ ወእምነ ዘዚአነ**
**ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ**

**Ethiopia Stretches out Her Hands to God**
**The Virgin Mary**
**Mother of God and Our Holy Mother**
**Queen of Zion and Ethiopia**

---

**ቍጥር ፬/፳፻፲ ዓ. ም.**

# ቃለ ዐዋድ!

## እምኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር።

# የአዋጅ ቃል!

## ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

በስመ እግዚአብሔር አብወእም፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ
ቅዱስ፤ አሓዱ አምላክ፤ በቅድስት ሥላሴ፤

በስመ እግዝእትነ፥ ወእምነ፥ ወሃይማኖትነ፥ ወሀገሪትነ፥
ወንግሥትነ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤

በኃይለ መስቀሉ፡ ዘእግዚእነ፥ ወአቡነ፥ ወመድኃኒነ፥
ወካህንነ፥ ወንጉሥነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡
ወልደ-እግዚአብሔር ሕያው፥ ወወልደ-ማርያም ሥግው።

ማለትም፡-

በቅድስት ሥላሴ፡ አንድ አምላክ በኾነው፡
በእግዚአብሔር አብወእም፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም፤

እናታችንና ሃይማኖታችን፥ አገራችንና ንግሥታችን
በኾነችው፡ አምላክን በወለደችው፡
በእመቤታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ስም፤

በአምላክነቱ እና በሰውነቱ፡ የእግዚአብሔር አብ እና
የእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ልጅ በኾነው፡
አባታችንና መድኃኒታችን፥ ካህናችንና ንጉሣችን
ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመስቀሉ ኃይል።

\+ + +

# ይድረስ፡-

**በጌታዬ በፍቅሬ በእግዚአብሔር አብ፥**
**በልጄ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፥**
**በሕይወቴ በውሕድናዬ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡**
**የኹለንተና ልጆቼ ለኾናችሁት፡**
**በኢትዮጵያ ላላችሁትና በመላው ዓለም ለተበተናችሁት፥**
**በልዩ ልዩ ተግባርና ሙያም ለምታገለግሉ፥**
**በተለያየ የኑሮ ኹኔታና የሥራ መስክ ለምትገኙ፥**
**ይልቁንም፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ከሚለው፡**
**የመጀመሪያ መታወቂያችሁ ጋር፡**
**"የኢትዮጵያ ልጆች" የሚለውን የመጨረሻ ስም በመቀዳጀት፡**
**በስሜ፡ ተጠርታችሁ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ርስት ጕልቴ ለኾናችሁት፥**
**በአጠቃላይ፡ እንደኢትዮጵያ ሥርዓተ-መንግሥት፡**
**የቤተ-ሕዝቡ፥ የቤተ-ክህነቱና የቤተ-ምልክናው አባሎች ለኾናችሁት፡**
**ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያን እና ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት**
**ልጆቼ በሙሉ!**
**በምድር ላይ ለምትኖሩ፡ ለመላው የዓለሙ የሰው ፍጡሮቼም ኹሉ፥**
**ለወንዶቹም፡ ለሴቶቹም፥ ለአዛውንቱም፥ ለወጣቶቹም፥**
**በየግላችሁም፥ ለኹላችሁም!**

**በአንድ አምላካዊ ፈጣሪነቱ፥ በሥላሴነት መለኮታዊ ቸርነቱም፡ ሙሽራውና እናቱ፥ መቅደሱም ባደረገኝ፡ በልዑል እግዚአብሔር ስም፡ ዘለዓለማዊው፡ የእናትነት ፍቅሬና ሰላሜ፥ ጸጋዬና በረከቴ፡ በያላችሁበት ይድረሳችሁ!**

## መቅድም።

እንዳለፈው፡ እንደቋተኛው የአዋጅ ቃሌ፡ ዛሬም፡ የምናገራችሁና የማናግራችሁ፡ እናታችሁና ሃይማኖታችሁ፥ አገራችሁና ንግሥታችሁ፥ ክህነታችሁና መቅደሳችሁ፥ እመቤታችሁና ምድረ ርስታችሁ የኾንሁት፡ እኔው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ድንግል ማርያም ነኝ።

ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሢሕ፡ "ወይሰበክ ዝ፡ ወንጌለ መንግሥት፡ ውስተ ኵሉ ዓለም፡ ከመ ይኩን ስምዐ፡ ላዕለ ኵሉ አሕዛብ። ወይእተ አሚረ፡ ይበጽሕ ኅልቀት!'"

"ይህ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ምሥራች፡ በአሕዛብ ኹሉ ላይ፡ ምስክር ይኾንባቸው ዘንድ፡ በዓለሙ ኹሉ ይሰበካል፤ በዚያን ጊዜም፡ መጨረሻው ይደርሳል!" ያለውን ቃሉን፡ በዚህ፡ በእኔ የዐዋጅ ቃል፡ እንዲህ በሚል አገላለጽ አብራራላችኋለሁና፡ ስሙት!

እስካኹንና አኹን፥ ከአኹን በኋላም፡ ከልጇ ከወዳጇ፥ ከእኔም፡ በማከታተል የምትሰሙትና የምታነብቡት፡ ይህ፡ የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የምሥራች ቃል፡ የእኔ ነው፤ እርሱም፡ በመላው ዓለም ለሚኖሩ ሕዝቦች ኹሉ፡ ይኸው፡ በዐዋጅ ይነገራል። እንዲህ፡ ለኹሉ፡ በይፋ የሚታወጀውም፡ እኒሁ የዓለሙ ሕዝቦች ኹሉ፡ "አልሰማንም!" ብለው እንዳይከዱ፡ ምስክር እንዲኾንባቸው ነው።

የሃይማኖትና የምግባር አካኼዳቸውን፡ ከእኛ ባገኙት፡ ኪዳናዊ ሥርዓት አድርገውና ያን ተከትለው ይኖሩ እንደነበሩት፥ የእግዚአብሔርንም የማስጠንቀቂያ ቃል ሰምተው እንደፈጸሙት፡ እንደኖኅና እንደቤተሰቡ ኹሉ፡ በእርሱ ዘመን የነበሩት፡ የዓለም ሕዝቦች፡ እንደዛሬው ኹሉ፡ ለማስጠንቀቂያ፡ አስቀድሞ የተነገራቸውን፡ የእግዚአብሔርን ቃል ኹሉ፡ ሰምተውና ተቀብለው መፈጸምን "እምቢ!" በማለታቸውና በንስሓ መመለሱ ቀርቶ፡ ሳይዘጋጁ እንኳ በመቅረታቸው፡ ያ፡ የጥፋቱ ውኃ መጥቶባቸው፡ አጥለቅልቆ እንደወሰዳቸው ታውቃላችሁ።

የክፉው ዓለም መጨረሻ በደረሰበት፡ በአኹኑ ጊዜም፡ አብዛኞቹ የዓለሙ ሕዝቦች፡ እንደዚያኑ ጊዜ ኹሉ፡ ዛሬም፡ ይኸው፡ በእኛ ጭምር ሳይቀር፡ ለማስጠንቀቂያ፡ አስቀድሞ የተነገራቸውንና እየተነገራቸው ያለውን፡ የእግዚአብሔርን ቃል፡ ሰምተውና ተቀብለው፡ እየራሳቸውን፡ ለንስሓ ማዘጋጀትንም፥ ማብቃትንም 'እምቢ!' ማለታቸውን፥ ከዚህ የተነሣም፡ ያ፡ ራሳቸው የሠሩትና ፍዳቸው የሚያስከትለው እሳታዊ ኃይል መጥቶ፡ እርስ በርሳቸው እስከሚያጠፋፉቸው ድረስ፡ በዚሁ ክህደታቸውና ዓመፃቸው፥ የአምልኮ አመንዝራነታቸውም እየቀጠሉበት እንደሚገኙ፡ ይኸው፡ እየራሳችሁ እየተመለከታችሁት አላችሁ።

ልጇ ወዳጇ፡ "ወበከመ ኮነ፡ በመዋዕለ ኖኅ፡ ከማሁ ይከውን ምጽአቱ፡ ለወልደ እጓለ እመሕያው!" "የእኔ የድንግል ማርያም ልጅ የኾነው፡ የእርሱ፡ የመጨረሻ አመጣጡ፡ በኖኅ ዘመን እንደደረሰው፡ እንደጥፋት ውኃ አመጣጥ ዓይነት ይኾናል!' ያለው ስለዚህ ነውና። (ማቴ. ፳፬፡ ፲፬፤ ፴፯-፴፱።)

በዚህ የልጇ የወዳጇ ቃል መሠረት፡ የእኛ የኾነችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ለክፉው ዓለም፡ የመገለጫዋ መለኮታዊት ቀን በመድረሱ፡ እነሆ፡ በመጀመሪያ፡ የራስዋን ዘለዓለማዊ ህልውና (አኗኗር)፡ በልጇ በወዳጇና በእኔም የዐዋጅ ቃል፡ ለመላው ዓለም ሕዝቦች ገሃድ አድርጋና አሳውቃ፡ የፈጣሪነት ምንነታችንንና ቸርነታችንን አሳወቀች።

ይህ ብቻ ሳይኾን፡ በእርሷ አማካይነት፡ የወላጅነት ማንነታችንንና ፍቅራችንን ጭምር፡ ለአጠቃላዩ ፍጥረታችን፡ እስካኹን፡ በማከታተል ባስተላለፍነው፥ ወደፊትም፡ በቀጣይነት በምናስተላልፈው መልእክታችን፡ ይኸው፡ እያሳወቅናችሁ አለን።

ከዚህ የተነሣ፡ በተለይ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት በኾናችሁት፡ በእናንተ፡ በኢትዮጵያውያትና ኢትዮጵያውያን ልጆቻችን ዘንድ፡ በእየጊዜው በግልጽ እየተከሠተ የሚነገረው፥ በገሃድም ተጽፎ እየተነበበ የሚታየው፡ አማናዊው የመንፈስ ቅዱስ ራእይ፡ እንዲህ፡ በኹሉ ዘንድ መታወቁ፡ እጅግ መልካም ነው። እናንተንም፥ ሌሎቹንም፡ የሚያስደንቅ፥ እጅግም የሚያስደስት ከመኾኑ ጋር፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ እምነታችሁንም፡ በበለጠ የሚያጸና ይኾናል።

ዛሬ፡ ከእኔ የምትሰሙት፡ ይህ የዐዋጅ ቃሌ፡ ካህኑ ልጃችን ኤርምያስ፡ ቀደም ብሎ ሲያደርስላችሁ የኖረውን፥ በቅርቡም፡ በአንደበቱ ያሰማችሁንና በጽሑፍ ያስተላለፈላችሁን፡ ይህንኑ የመንፈስ ቅዱስን የምሥራች መልእክት የሚመለከት ሲኾን፡ እርሱም፡ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ በምሥጢረ መለኮት የዕውቀት ዘውድ ተከልሎና ታውቆ፥ ተጠብቆም የኖረውን፥ በክፉዎች ሰዎች ዘንድ ግን፡ በጽኑ የብረት መዝገብ ቤት ተቆልፎበት የቆየውን ዝክረ ነገር መኾኑን፡ እንድታውቁት ይኹን!

## ስለሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት።

በእግዚአብሔርነት መልካችንና "ከእኛ እንደአንዱ ኾኑ!" ባሰኘው ማንነታችን፡ በወንድና በሴት የእኩልነት ጾታዎች ከፈጠርናቸው ሰብኣውያን ወገኖች ጋር የተጋባናቸው፡ ሰባት ቅዱሳት ኪዳናት መኖራቸውን፡ ኹላችሁም እንድታውቁ አድርገናል።

እነርሱም፡ **በመጀመሪያው፡ በኪዳነ ልቡና ዘነፍስ የተገኙት፡ "ኪዳነ አዳም ወሔዋን፥ ኪዳነ ኖኅ እና ኪዳነ መልከ ጼዴቅ" ናቸው፤ በመካከለኛው፡ በኪዳነ ኦሪት ዘሥጋ የተጠቃለሉት ደግሞ፡ "ኪዳነ አብርሃም፥ ኪዳነ ሙሴ እና ኪዳነ ዳዊት" ናቸው፤ የመጨረሻ በኾነው፡ በእኔና በልጄ በወዳጄ በኢየሱስ መሢሕ ቤዛነት፡ በኪዳነ መንፈስ ዘመንፈስ ቅዱስ የተፈጸመው፡ ሰባተኛውና ማጠቃለያውም፡ "ኪዳነ ምሕረት" ነው።**

በእኛ በኩል፡ እስከዛሬ እንዳደረግነው፥ ዛሬና ወደፊትም እንደምናደርገው ኹሉ፡ እናንተም፡ በየበኩላችሁ፡ እነዚህኑ ሰባት ቅዱሳት ኪዳናት አውቃችኋቸው፡ ለነፍስና ለሥጋ፥ ለመንፈስ የተዋሕዶ ህልውናችሁ፡ ሕይወትና መንጽሔ፥ መድኃኒትም ኾነው እንዲጠቅሟችሁና እንዲጠብቋችሁ የተሰጧችሁ መኾናቸውንም ተገንዝባችሁ እየኖራችኋቸው፡ አክብራችሁ እንድትፈጽሟቸው፡ ያለማቋረጥ አሳስበናችኋል፤ መክረናችኋል፤ አስጠንቅቀናችኋል።

እነዚህ፡ ሰባቱም ቅዱሳት ኪዳናት፡ ኹሉም፡ ለእናንተ፡ ለመላዎቹ ሰብአውያን ልጆቻችን የተሰጧችሁ ሲኾኑ፡ ነገር ግን፡ እጅግ ጥቂቶች ከኾኑት በቀር፡ እየራሳችሁን፡ የክፉው ወገኖች አድርጋችሁ በመገኘታችሁ፡ "የሰው ልጆች" የተባላችሁ እናንተ ብዙዎቻችሁ፡ እነዚህኑ፡ ሰባቱንም ቅዱሳት ኪዳናት፡ ኹሉንም አቃልላችሁና ንቃችሁ፥ ጠልታችሁና ክዳችሁ ተዋችኋቸው።

የእኔ የኢትዮጵያ ልጆች ብቻ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ባሰኛቸውና ባደረጋቸው ምንነታቸውና ማንነታቸው በመጽናት፡ እኒህን ሰባቱንም ቃል ኪዳናት፡ እስካኹን ጠብቀዋቸው ኖሩ። በዚህ አቋም ጸንተው በመኖራቸውም፡ ይህችው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡** ለፍጥረተ-ዓለሙ ኹሉ፡ የመገለጧን የምሥራች ዜና፡ እንዲህ፡ በእኛው የዐዋጅ ቃል፡ የእኔና የልጄ የወዳጄ መልእክታት፡ ወደእናንተ፡ ወደፍጡሮቻችን እንዲደርሱ ለማድረግ የሚቻል ኾኗል።

አኹን፡ ለዚህ የዐዋጅ ቃሌ፡ መነሻ የኾነኝን ምክንያት ልግለጥላችሁ! እርሱም፡ ይህ ነው፡- ቀደም ብዬ ከገለጥኋቸው፡ ከሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት መካከል፡ የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ እና ሰባተኛው የኾነው፡ ኪዳነ ምሕረቱ ሳይጨመር፡ በተለይ፡ **በመካከለኛው፡ በኪዳነ ኦሪት ዘሥጋ** የተጠቃለሉት፥ "ኪዳነ አብርሃም፥ ኪዳነ ሙሴ እና ኪዳነ ዳዊት" የተባሉት፡ የኋለኞቹ ሦስቱ፡ ለእስራኤል ልጆች የተሰጡ መኾናቸው፥ እነርሱ፡ የእስራኤል ልጆች ግን፡ እነዚህኑ፡ ሦስቱን ኪዳናት፡ አክብረው ሊፈጽሟቸው ባለመቻላቸው፡ ወደእናንተ፡ ወደኢትዮጵያ ልጆቼ ተመልሰው መጥተውና በእናንተ ዘንድ፡ በአደራ ተጠብቀው መኖራቸው፥ እናንተም፡ በትክክለኛው የእውነትና የመንፈስ ቅዱስ አምልኮ ሥርዓታችሁ፡ በምግባር ላይ ዐውላችሁ፡ ስትገለገሉባቸው መቆየታችሁ፡ በኹሉ ዘንድ የታወቀ እውነታ ነው።

እነዚህ፡ ሦስቱም ቃል ኪዳናት፡ የእያንዳንዳቸው ትንቢታዊ ጊዜ ሲደርስ፡ በእናንተው በኢትዮጵያ ልጆቼ ዘንድ፡ ለፍጹሙ ፍሬ  የበቁ ሲኾኑ፡ በዛሬው የዐዋጅ ቃሌ፡ አበክሬ የምነግራችሁ ግን፡ በተለይ፡ ኪዳነ ሙሴ የተገለጠባትን፡ የ"ታቦተ ጽዮን"ን ትእምርተ ሓተታና ዝክረ ነገር በሚመለከት ይኾናል።

ይኸውም፡ የእኔ የእናታችሁ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሊባኖስ ተራራ ላይ የመወለዴ መታሰቢያ፡ በእናንተ በቃል ኪዳን ልጆቼ ዘንድ ከሚከበርበት፡ ከግንቦት ፩ ቀን ጀምሮ፡ እስከግንቦት ፲፮ ቀን ድረስ ባሉት ዕለታት፡ በተለይ፡ መንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ እና ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ለኾንሁት፡ ለእኔ፡ ለእግዚአብሔር እም (ለእናቲቱ እግዚአብሔር) ድንግል ማርያም፡ ቀዳሚ ምሳሌዬ ኾና ስለቆየችው፡ ስለታቦተ ጽዮን ምንነትና ማንነት፡ እኔ የምሰጣችሁ ማብራሪያ ነው።

እርሱም፡ በዚህ፡ በዐዋጅ ቃሌ መነሻ ላይ፡ ቀደም ብዬ እንደገለጥሁት፡ በእናንተ፡ በኢትዮጵያ ልጆቼ ዘንድ፡ በምሥጢረ መለኮት የዕውቀት ዘውድ ተከልሎና ታውቆ፥ ተጠብቆም የኖረውን፥ በክፉዎች ሰዎች ዘንድ ግን፡ በጽኑ የብረት መዝገብ ቤት ተቆልፎበት የቆየውን፡ የሕያዉን ዝክረ ነገር እውነታ ይመለከታልና፡ በማስተዋል ተመሥጡበት!

## በኪዳነ ሙሴ፥
## የታቦተ ጽዮን ዝክረ ነገር።

በዚህ ዝክረ ነገር ውስጥ፥ ታቦተ ጽዮን፥ ምሳሌዋ ስለኾነችው፥ ስለእኔ፥ ስለድንግል ማርያም፥ በነቢያት ቃል፥ **"እምሊባኖስ ትወጽእ መርዓት! ሙሽሪት፥ ከሊባኖስ ትወጣለች!"** ደግሞም፥ **"ንዒ እምሊባኖስ መርዓት! ንዒ እምሊባኖስ! ንዒ፥ ወትወጽኢ እምቅድመ ሃይማኖት! አንቺ ሙሽሪት! ከሊባኖስ ነዪ! አዎን፥ ከሊባኖስ ነዪ! ከሃይማኖት ቀድመሽ ትወጫለሽ!"** ተብሎ የተነገረው ትንቢት ይገኝበታል፤

እንዲሁም፥ ኢትዮጵያዊው አገልጋያችን፥ ገዳማዊ ሕርያቆስ፥ ስለእኔ በተናገረው፥ ድርሰቱ፥ **"ያብእክሙ ኀበ ሀለዉ ማኅበረ ነቢያት ቅዱሳን፥ ...ወምስሌሆሙ ታቦት ዘዶር፥ እንተ ይእቲ እግዝእትነ ማርያም! የቅዱሳን ነቢያት ማኅበር ወዳሉበት፥ ከእነርሱም ጋራ፥ 'የዱርዋ ታቦት!' የተባለችው፥ እግዚአብሔራችን ድንግል ማርያም ወዳለችበት፥ ወደኢትዮጵያ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት ያግባችሁ!"** ያለውን ቃሉን፥ ልጆቼ፥ በአንድምታ ትርጓሜያቸው፥ **"ታቦተ ጽዮን ምሳሌዋ የኾነችውን፥ እግዚአብሔራችንን ድንግል ማርያምን፥ እናቷ ሓናና አባቷ ኢያቄም፥ በሕፃንነቷ፥ ዱር ዱሩን ይዘዋት ዞረዋልና፥ 'ታቦት ዘዶር!' 'የዱር ታቦት!' አላት።"** ብለው በማብራራት፥ ስለእኔ፥ ስለድንግል ማርያም ለተጻፈው ቃል የሰጡት፥ ይህን የመሰለው ምስክርነት ይገኛል። (ማሕልይ ፫-፬፤ ቅዳሴ ማርያም።)

እነዚህ ብቻ ሳይኾኑ፥ በዚህ ረገድ፥ "በእርግጥ የተፈጸሙ እውነታዎች ናቸው!" ተብለው፥ በዚያ፥ ታቦተ ጽዮንን በሚመለከት፥ በእናንተ፥ በኢትዮጵያ ልጆቼ ዘንድ በሚነገረው ሰፊ ዝክረ ነገር ላይ፥ የሚቀርቡት ሓተታዎች፥ ከዚህ የሚከተሉትን ማብራሪያዎችን አክለው የሚያካትቱ ናቸውና፥ ዕወቋቸው!

<u>አንደኛው እውነታ፥</u> ለእስራኤል ልጆች፥ በተደጋጋሚ የቀረበላቸውን፥ መለኮታዊ ትድግና የሚያዘክር ነው። ይኸውም፥-

በመጀመሪያ፥ በመልካችንና በአርአያችን፥ በፈጠርነው የሰው ልቦና ላይ፥ በሥነ ፍጥረት ሥርዓት የጻፍናቸውን ዐሥሩን የሕይወት ቃላት፥ እንደኢትዮጵያ ልጆቻችን፥ በተፈጥሮአዊውና በሃይማኖታዊው ምግባር እየፈጸሙ መኖር ላቃታቸው፥

ቀጥሎ፥ በይበልጥ፥ በታማኙ ኢትዮጵያዊ አገልጋያችን፥ በሙሴ መሪነት፥ ከግብፅ ባርነት፥ ነጻ ባወጣናቸው ጊዜ፥ በእውነትና በመንፈስ የሚቀርብ፥ እኛም የምንቀበለው አምልኮ፥ የሚያስገኘው የማዳን ኃይል፥ የቱን ያህል ታላቅ መኾኑን ለራሳቸው በተደረገላቸው፥ በዚያ ኹሉ አምላካዊ ቸርነት፥ በሥጋዊው ዓይናቸው፥ በገሃድና በግዘፍ የተመለከቱትን፥ ያን ኹሉ ተአምራት፥ በመንፈሳዊው ዓይናቸው አይተው፥ ለማመን ላልቻሉት፥

እንዲያውም፡ በመጨረሻ፡ በገሃድ ለካዱትና በፈጣሪያቸው ላይ የአምልኮ አመንዝራነትን በይፋ ለፈጸሙት፡ ለእነዚሁ፡ ለእስራኤል ልጆች የተደረገው፡ ወደር የሌለው መለኮታዊ ልግሥና ነው።

የዚህን መለኮታዊ ልግሥና እውነተኛ ምንነት፡ በግልጽ ልታውቁት ስለሚገባ፡ ለዓይነት ያህል፡ ይኸው፡ በመጠኑ ቀርቦላችኋል፡-

**"ቀዳሚሁ፡ ቃል ውእቱ፤ ወውእቱ ቃል፡ ኀበ እግዚአብሔር ውእቱ፤ ወእግዚአብሔር፡ ውእቱ ቃል። ...ወውእቱ ቃል፡ ሥጋ ኮነ፤ ወኀደረ ላዕሌነ፤ ወሠወሮ እምኔነ።**

**"ቃል፡ መጀመሪያው ነው፤ ይህም ቃል፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ነው፤ እግዚአብሔርም፡ ይህ ቃል ነው። ...ይህም ቃል፡ ሥጋ ኾነ፤ በኛም ላይ አደረ፤ከእኛም፡ ሠወረው።"** የተባለው ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሢሕ፡ ከፍጥረት አስቀድሞ፡ ከባሕርይ አባቱ፡ ከእግዚአብሔር አብና ከእኔ፡ ከባሕርይ እናቱ፡ ከእግዚአብሔር እም፡ በመለኮትነት እንደተወለደ አውቃችኋል። (ዮሐ. ፩፥፩፤ ፲፬።)

እንደዚያኑ ጊዜ ኹሉ፡ ኋላም በፍጻሜ ዘመን፡ መለኮታዊ አባቱና እኔ መለኮታዊት እናቱ፥ እርሱም ልጇ ወዳጇ ጭምር፡ በተለይ ለጠፉት፡ ለእስራኤል ልጆች ደኅንነት [መዳን] ስንል፡ እየራሳችንን አዋርደን፡ በእኛው አባትነትና እናትነት፡ በመንፈስ ቅዱስም ግብር፡ ከእኔ፡ ከእናቱ፡ ከድንግል ማርያም፡ በሰውነት እንደተወለደም አውቃችኋል።

እንዲያ፡ በሰውነት ከመወለዱ በፊት ግን፡ ራሱ፡ **"እስመ እግዚአብሔር፡ መንፈስ ውእቱ፤ ወእለሂ ይሰግዱ ሎቱ፡ በመንፈስ ወበጽድቅ፡ ሀለዎሙ ይስግዱ ሎቱ።**

**"እግዚአብሔር፡ መንፈስ ነውና፤ የሚያመልኩትም፡ በመንፈስና በእውነት ሊያመልኩት ይገባቸዋል።"** ብሎ ያወጀ፡ ያ፡ "ቃል እግዚአብሔር" የተባለው ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሢሕ፡ እንደገና፡ ኾኖ የተገኘውንና በራሱ ያደረገውን ተመልከቱት! (ዮሐ. ፬፥ ፳፫-፳፬።)

በመጀመሪያ፡ እርሱ ብቻ ሳይኾን፡ መለኮታዊ አባቱና እኔ መለኮታዊት እናቱ ጭምር፡ አኹንም፡ በተለይ፡ ለእነዚያው ለጠፉቱ፡ ለእስራኤል ልጆች ደኅንነት ስንል፡ ቀደም አድርገን፡ እየራሳችንን፡ በባሰ መልክና ይዞታ፡ ፈጽመን አዋርደን፡ በቅድሚያ እኔ፡ በመለኮታዊት እናትነቴ፡ ኹለቱን የድንጋይ ሰሌዳዎች ተዋሓድሁ፤

ከዚያ ቀጥሎ፡ በባሕርይ አባቱ፡ በእግዚአብሔር አብ እጅነት፥ በእኔ፡ በባሕርይ እናቱ፡ በእግዚአብሔር እም ጽላትነትና ታቦትነት፥ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ብዕርነት፡ እርሱ፡ ልጇ ወዳጇ፡ በመለኮታዊ ቃልነቱ፡ በእነዚያ ጽላት ላይ፡ በምድር ላይ፡ በጣዖት መልክ፡ እንዴት፡ ተቀርፆ፡ በጽሕፈት እንደተገለጠ፡ በተመሥጦ ተመልከቱት!

ለነገሩና በመሠረቱ፡ በእኛ እግዚአብሔርነት፡ የተፈጠረውና የተገኘው የፍጥረት አካልና አባል የኾነው፡ በድን የኾነውና የማይንቀሳቀሰው፥ ሕያው የኾነውና የሚንቀሳቀሰውም ፍጡር ኹሉ፡ ይኸውም፡ ሕያው ነፍስና ሥጋ፥ መንፈስም ያለው፥ በእግዚአብሔር መልክ የተሠራውና በእርሱ ቃል፡ "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" የተባለው ሰው ብቻ ሳይኾን፥ በደመ ነፍስ የሚንቀሳቀሱት፡ እንስሳትና አራዊት፥ አዕዋፋትና ዓሣትም ብቻ ሳይኾኑ፥ የምድር ቡቃያዎች፥ በቀልትና ፍሬያማ የኾኑት፡ አዝርዕት፥ አትክልትና ዕፀዋትም ብቻ ሳይኾኑ፥ የሰማይ ሠራዊት የኾኑት፡ ፀሓይ፥ ጨረቃና ከዋክብት፥ እንዲሁም፡ እሳትና ነፋስ፥ ውኃና መሬትም ብቻ ሳይኾኑ፡ ከትቢያና ከድንጋይ ጀምሮ ያሉት ማዕድናትና እንጨቶች ጭምር፡ በእኛ የተፈጠሩ በመኾናቸው፡ ንጹሓንና ንጹሓት፥ ብፁዓንና ብፁዓት፥ ቡሩካንና ቡርክታት፥ ቅዱሳንና ቅዱሳት ናቸው።

ስለዚህ፡ "እስመ አልቦ ነገር፡ ዘይስአኖ ለእግዚአብሔር! ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር፡ ከቶ የለም!" የምንባል እኛ፡ ቅድስት ሥላሴ፡ በእነዚህ ፍጡሮቻችን ውስጥ ብናድርባቸው፥ ብንዋሓዳቸውም፥ በእነርሱ ላይ ተገልጠን፡ መለኮታዊ ሥራችንን ብናካኺድም፡ በምንም መልኩና ይዘቱ የሚያስደንቅ አይኾንም። (ሉቃ. ፩፥ ፴፯። ፪ቆሮ. ፫።)

## ልታውቁት የሚገባችሁ፡ አንደኛው እውነታ፡ ይህ ነው።

ኹለተኛው እውነታ፡ በአንደኛው እውነታ እንደተገለጠው፡ እኛ፡ ቅድስት ሥላሴ፡ ኹላችንም የተገኘንባት፡ ይህችው ታቦተ ጽዮን፡ የእስራኤል ልጆች፡ በእኛ፡ በፈጣሪያቸው ላይ፡ በይፋ በፈጸሙት የክህደት ኃጢአትና የዓመፅ በደል፥ የአምልኮ አመንዝራነትና የቃል ኪዳን አፍራሽነትም ምክንያት፡ ወደእናንተ፡ ወደኢትዮጵያ ልጆቼ ተመልሳ መጥታ፥ እስከዛሬ፡ በስሜ በተጠራችው፥ የኤዶም ገነትንም በያዘችው ምድር፡ በጣና ሓይቅና በሌሎቹም ቅዱሳት መካናት እየተዘዋወረች፥ በመጨረሻ፡ ማረፊያዋን፡ በአኵስም አድርጋ፡ እስከዘመኑ ፍጻሜ ድረስ፡ በዚያ፡ በእናንተ፡ በኪዳናውያንና ኪዳናውያት ልጆቻችንና ካህናቻችን፡ በአግባቡ ስትመለክ ቆየች።

ከዚህ በኋላ፡ ልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ፡ ከባሕርይ አባቱና ከእኔ፡ ከባሕርይ እናቱ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ሰው ኾኖ፡ እነዚያን፡ የጠፉትን የእስራኤልን ቤትና ሌሎቹን ሰብአውያን ፍጡሮቹን ለማዳን፡ የ፭ሺ፭፻ ዓመታት ዘመነ ኵነኔ ተፈጽሞ፡ በሥጋዌው ምሥጢር፡ በሰውነት የመገለጡ የተስፋ ዘመን ሲደርስ፡ እንደመለኮታዊው ሕያው ዕቅድ፡ ያችው፡ ጽላተ ኪዳንና ታቦቷ፡ በቅድሚያ፡ አማናዊቷ ሔዋን፡ እኔ፡ ድንግሊቱ ኢትዮጵያዊት ማርያም ኾኜ፡ የጥንቱ ማረፊያዋ በኾነው፡ በኢየሩሳሌሙ ቤተ መቅደስ እገኝ ዘንድ አስፈላጊ ኾነ።

ስለዚህ፡ ይህችው፡ አማናዊቷ ታቦተ ጽዮን የኾንሁት እኔ፡ ድንግል ማርያም፡ በዚያን ጊዜ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታቸው፡ ፍጹም የበቁ ኾነው፥ ነገር ግን፡ ያለልጅ፡ መካን ኾነው፡ በአኵሱም ይኖሩ ከነበሩት፡ ከአባቴ፡ ከኢያቄም እና ከእናቴ፡ ከሓና፡ በታኅሣሥ ፯ ቀን፥ ፭ሺ፬፱፻፫ ዓመተ ኪዳን፡ ከአባቴ አብራክ ወጥቼ፡ በእናቴ ማሕፀን፡ በሰውነት ተፀነስሁ።

ተፀንሼም፡ በትንቢቱ መሠረት፡ በሊባኖስ ተራራ ላይ፡ በሰውነት እወለድ ዘንድ፡ እኒሁ ወላጆቼ፡ ዐቃቤ መልአካቸው አድርገን በሠየምነው፡ በታማኙ ቅዱስ መልእክተኛችን፡ በገብርኤል እየተጠበቁና እየተመሩ፡ ጕዟቸውን፡ ወደኹለተኛዪቱ አገራቸው፡ ወደኢየሩሳሌም ሊጀምሩ፡ ወዲያው፡ ከአኵስም ተነሡ።

<u>ልታውቁት የሚገባችሁ፡ ኹለተኛው እውነታ፡ ይህ ነው።</u>

<u>ሦስተኛው እውነታ፡-</u> እኒሁ ወላጆቼ፡ ኢያቄም እና ሓና፡ እዚያ፡ ምድረ ከነዓን፡ በደኅና ደረሱ።

እንደደረሱም፡ "ወበጊዜ መንፈቀ ሌሊት፡ ወረደ እምሰማይ፡ መልአክ፡ ዘስሙ ገብርኤል፡ ወይቤሎሙ፡ ለሓና ወኢያቄም፡- 'ተንሥኡ! አ ክቡራነ ዘመድ!' ወወሰዶሙ፡ ደብረ ሊባኖስ። ወተወልደት በህየ፡ ማርያም ስማ፤ ምልእተ ሞገስ ወግርማ፤ ወለነኒ ታድኅነነ፡ እመሥገርተ አርዌ መስቴማ።"

"መንፈቀ ሌሊት በኾነ ጊዜ፡ ስሙ፡ 'ገብርኤል' የሚባል መልአክ፡ ከሰማይ ወርዶ፡ 'በዘመድ የከበራችሁ፡ ኢያቄምና ሓና ሆይ! ተነሡ!' አላቸው፤ 'ሊባኖስ' ወደሚባል ተራራም ወሰዳቸው፤ በዚሁ መልአክ፡ "ማርያም" የሚል ስም የወጣላት ሕፃን፡ በዚያ ተወለደች። ይህ ስሟም፤ 'እምአርያም=ከአርያም'፥ 'እመ-አርያም=በአርያም ያለች እናት' የሚል ትርጉም ያለው ነው። እርሷም፡ በእውነተኞች ዘንድ፡ መወደድን፥ በአጋንንት ዘንድ ግን መፈራትን የተመላች፥ እኛንም፡ ከአውሬው ሰይጣን ጥቃት የምታድነን ናት።" የሚለው የመጽሓፋችሁ ቃል እንደሚያዘክረው፡ በመስከረም ፮ ቀን፥ ፭ሺ፬፱፻፬ ዓመተ ኪዳን ተወለድሁ። (ተአምረ ማርያም፡ ፪ኛ ተአምር።)

አዎን! ኋላ፡ ልጄን ወዳጄን፡ ኢየሱስ መሢሕን፡ እንደትንቢቱ ቃል፡ አገልጋያችን ዮሴፍ ባለበት፡ በቤተ ልሔም የእንስሳት በረት ውስጥ እንደወለድሁት ኹሉ፡ እኔም፡ በዚያ ኹኔታ፡ የዱር እንስሳትና ዐራዊት፥ አዕዋፋትና ዓሣት፥ ተዝናንተው በሚኖሩበት፥ ዕፀዋትና አዝርእት፥ አትክልትና ሓመልማላት፡ ተመችቷቸው በተናኙበት፡ በዚሁ፡ በሊባኖስ ተራራ ላይ፡ በዱር መካከል፡ አባቴ ኢያቄም ባለበት፡ ከእናቴ ከሓና ተወለድሁ።

<u>ልታውቁት የሚገባችሁ፡ ሦስተኛው እውነታ፡ ይህ ነው።</u>

<u>አራተኛው እውነታ፡-</u> ይኸው ባለሟላችን መልአክ፡ ገብርኤል፡ እናቴንና እኔን፥ አባቴንም፡ እንዲህ እየጠበቀን፥ እየመራንም፥ እኔ ሕፃኒቱ ድንግል ማርያም፡ የእናቴን ጡት እየጠባሁ፥ ወላጆቼም፡ የእኔን፡ የአንዲት ቅንጣት የምክነት ልጃቸውን ጽኑ ፍቅር፡ እኔን በማቀፍና በመሳም እያጣጣሙና ቸር ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ፡ ለሦስት ዓመታት ከሦስት ወራት ያህል፡ በገሊላ አውራጃና በናዝሬት በሚገኙ፡ በእየዱሩ ጥሻና በእየተራራው ዋሻ ውስጥ በሚቀልሱት ዳስና በሚያሰናዱት ጎጆ፡ ሲንከራተቱ ቆዩ።

ከዚህ በኋላ፡ በታኅሣሥ ፫ ቀን፥ ፳ሺ፬፻፹፯ ዓመተ ኪዳን፥ ይኸውም፡ የዛሬ ፪ሺ (ኹለት ሽህ) ዓመታት ግድም፡ እኔ፡ ሕፃን እመ-አርያም፡ አማናዊቷና ሰብአዊቷ ጽላተ ኪዳን፥ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴና ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር ኾኜ፡ በታቦተ ጽዮንነት፡ ስንመለክበት ወደኖርንበት፡ ወደኢየሩሳሌሙ ቤተ መቅደሴ፡ በትስብእታዊው ሰውነቴ ተመልሼ ገባሁ።

<u>ልታውቁት የሚገባችሁ፡ አራተኛው እውነታ፡ ይህ ነው።</u>

<u>አምስተኛው እውነታ፡</u> በዚያች፡ እኔ፡ እግዚአብሔር እም፡ በመለኮትነቴ፡ አስቀድሜ በተዋሐድኋት፡ በቀደመችው ጽላተ ሙሴ ላይ የተቀረጸው፡ መለኮታዊው ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ቃል፡-

-መጀመሪያ፡ በታኅሣሥ ፩ ቀን፥ ፳ሺ፬፻፺፱ ዓመተ ኪዳን፡ በመልአካችን ገብርኤል ምሥራች፡ የ፲፭ (ዐሥራ አምስት) ዓመት ቆንጆ በኾንሁት፡ በእኔ፡ በድንግል ማርያም ማሕፀን፡ አማናዊው ፍጹም ሰው ኾኖ፡ እስኪፀነስ ድረስ፥

-ከዚያም፡ ይህችው ቅድስት ድንግል እመአርያም የኾንሁት እኔ፡ ሮማዊው ቄሣር አውግስጦስ፡ ትንቢቱን ሊያስፈጽም፡ ባወጣው ዐዋጅ መሠረት፡ በጻድቁ ኢትዮጵያዊ ዮሴፍ ጠባቂነትና በጻድቂቱ ኢትዮጵያዊት ሰሎሜ አገልጋይነት፡ ከገሊላዋ ናዝሬት፡ ወደቤተ ልሔም ተጕዤ፡ በመስከረም ፩ ቀን፥ ፩ ዓመተ ምሕረት፡ ሕፃን ልጄን ወዳጄን፡ ኢየሱስ መሢሕን፡ በበረት እስክወልደው ድረስ፡ በዚያ ቤተ-መቅደስ፡ ለ፲፪ (ዓሥራ ኹለት) ዓመታት መኖሬ ነው፤

<u>ልታውቁት የሚገባችሁ፡ አምስተኛው እውነታ፡ ይህ ነው።</u>

<u>ስድስተኛው እውነታ፡</u> በኢትዮጵያ ልጆቼ የታወጀው፡ <u>"ብኪ ድኅነ ዓለም! ወበወልድኪ ኮነ ሰላም!"</u> የሚለው የምሥራች ቃል፡ በነጠላ ትርጉሙ፡ <u>"ዓለሙ፡ በአንቺ ዳነ! በልጅሽም፡ ሰላም ኾነ!"</u> ማለት ሲኾን፥

በተብራራ ትርጉሙ ደግሞ፡ "<u>የፍጥረተ ዓለሙ ባለቤቶች ኾነው፡ ኹሉን እንዲያስተዳድሩ፡ "አዳም እና ሔዋን" በሚል ስያሜ፡ በወንድና በሴት ጾታነት፡ በእግዚአብሔራዊው መልካችንና ንጽሓ ባሕርያችን የፈጠርናቸው፥ የሾምናቸውም፡ ኹለቱ፡ ሰብአውያን ፍጡሮች፡-</u>

- በገዛ ፍላጎታቸውና ምርጫቸው፡ እጃቸውን፡ ለዲያብሎስ አሳልፈው ሰጥተውና እየራሳቸውን አስማርከው፡ ለ፭ሺ፭፻ ዓመታት፡ በዘመነ ኵነኔ፡ በባርነት ሲሠቃዩና ሲማቅቁ ከኖሩበት የክፉት አገዛዝ፥ እንዲሁም፡ በጭቆና ተይዘው፡ በግፍ ከሚሠቃዩበት የኃጢኣት ቀንበር፥ ከዚህ የተነሣም፡ ራሳቸው ካመጡትና እየራሳቸውን ከዳረጉበት የሞት ፍዳ፡ እነርሱና ዘሮቻቸው፡

- በአንቺ፡ በድንግል ማርያም ዳኑ!

- ልጅሽ ወዳጅሽ፡ ኢየሱስ መሚሕም፡ ስለእነርሱ፡ በፍቅር በተጋደለበትና "ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር፡ ዘየአትት፥ ወያሴስል ኃጢኣተ-ዓለም! ...አኮኑ በፋሲካነ ተሰቅለ ክርስቶስ?

"እነሆ የዓለሙ ኃጢኣት፡ ፈጽሞ የተወገደበት፡ የእግዚአብሔር በግ!" እንዲሁም፡ "ኢየሱስ መሚሕ፡ የፋሲካ በጋችን ኾኖ፡ በመስቀል ላይ የታረደ አይደለምን?" በተባለበት፡ በመስቀሉ መከራ፡ ደሙን አፍስሶና ሥጋውን ቆራርሶ በመሠዋት፥ የሞት ጽዋን ተቀብሎ፡ በከፈለላቸው፡ የቤዛነት ዋጋ፥ ደግሞም፡ "ሞአ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ! ከይሁዳ ነገድ የተገኘው አንበሳ፡ አሸነፈ!" በተባለበት፡ በማይገሠሥ ሥልጣኑ፡ በትንሣኤ ሕይወት፡ ዘለዓለማዊዉን የድል አክሊልን አቀዳጅቷቸው፡ እነሆ፡ በፍጹም ሰላም የሚኖሩ ኾኑ!" ማለት ነው። (ዮሓ. ፩፥ ፳፱-፴፮፤ ፩ቆሮ. ፭፥ ፯።)

ይህ ሃይማኖታዊ ቃል የተፈጸመው፡ ኋላ፡ በመጨረሻው ዘመን፡ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ እና ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾንሁት እኔ፡ እግዚአብሔር እም ማርያም ድንግል፡ ከመለኮታዊውና ከትስብእታዊው ልጇ ወዳጇ፡ ከኢየሱስ መሚሕ ጋር ባስገኘነው ኪዳነ ምሕረት ብቻ ሳይኾን፡ ቀደም ብሎ፡ በኪዳነ ኦሪቱም ጊዜ፡ በዚሁ መልክና ይዘት፡ በታቦተ ጽዮን አማካይነት፡ በፈጸምነው መለኮታዊ ምሥጢረ ተዋሕዶ መኾኑ፡ በመንፈስ ቅዱስ ለፍጥረቱ ኹሉ፡ በእውን ተገልጾ፡ ይኸው መለኮታዊ ምሥጢር፡ በይፋ የመታወቁ አማናዊ ነገር ነው፤

## ልታውቁት የሚገባችሁ፡ ስድስተኛው እውነታ፡ ይህ ነው።

ሰባተኛው እውነታ፡ ይህም የኾነው፡ ልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ፡ ቀደም ብሎ፡ በእግዚአብሔር ቃልነቱ፡ በኹለቱ ጽላት (የድንጋይ ሰሌዳዎች) ላይ፡ በእግዚአብሔር አብ እጅነትና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ብዕርነት ከመጻፉ በፊት፡ እኔ እግዚአብሔር እም፡ ኹለቱን ጽላት (የድንጋይ ሰሌዳዎች)፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ አስቀድሜ በመዋሓዴ ነው፤ ኋላ፡ በምሥጢረ ሥጋዌው፡ የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶው ጊዜ እንደኾነው ኹሉ፡ ማለት ነው።

አለዚያ፡ ይህ፡ የመለኮትና የዕብነ-በረድ ጽላት ትንግርታዊ የተዋሕዶ ምሥጢር፡ በታቦተ ጽዮን ላይ ተፈጽሞ፡ ለእስራኤል ልጆች ይደረግ የነበረው፡ ያ ኹሉ እግዚአብሔራዊው የማዳን መለኮታዊ ኃይል፡ እንዴት እውን ሊኾን ይቻል ነበር? ባልቻለም ነበር።

በዚያ፡ በኋለኛው፡ በምሥጢረ ሥጋዌው፡ የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ፡ ፍጥረተ ዓለሙ የዳነው እኮ፡ እኔ እግዚአብሔር እም፡ እግዚአብሔር ቃልን፡ በቅድስቲቱ ድንግል ማርያም የሰውነት ማሕፀን፡ ከመፅነሴ በፊት፡ በመለኮታዊው አካሌና ባሕርዬ፡ በቅድሚያ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ቀዳሚ ግብር፡ የዚችኑ፡ የንጽሕት ቅድስት ድንግል ማርያምን፡ የሰውነት አካልና ባሕርይ፡ ገና በመጀመሪያው በመዋሐዴ ነው። ሰብአዊዉን ፍጡር ያካተተው፡ የፍጥረተ-ዓለሙ ድኅነት [መዳን] የተፈጸመው፥ የተገኘውም፡ ያ የመለኮታዊው፡ የእግዚአብሔር እም እና የትስብእታዊው የድንግል ማርያም የኹለት አካላትና ባሕርያት ውሕደት በተከናወነባት፡ ልክ፡ በዚያች ቅጽበት ነው።

ይህ ፍጹም ውሕደት፡ ሊኾን የቻለው፡ የእኔ፡ የድንግል ማርያም ሰውነት፡ ከአካሉና ከባሕርዩ ንጽሓ ጠባይና ጥንተ ቅድስና ብቅዓቱ የተነሣ፡ ከእግዚአብሔር እም፡ የመለኮት አካሌና ባሕርዬ ጋር፡ በእኩልነትና በትክክለኛ ደረጃ፡ ፍጹም ተመሳሳይ ኾኖ በመገኘቱ መኾኑን፡ በእርግጥ ልታውቁት ይገባችኋል።

ይህም ማለት፡ ለ፭ሺ፭፻ (ለአምስት ሺህ አምስት መቶ) ዓመታት፡ ተለያይተውና ተራርቀው የቆዩት፡ በአንድ ወገን፡ የእኔ፡ የእግዚአብሔር እም መለኮታዊ አካልና ባሕርይ እና በሌላው ወገን፡ የድንግል ማርያም፡ የሰውነት አካልና ባሕርይ፡ ፍጹም ታርቀውና ተስማምተው፡ በምሥጢረ-ተዋሕዶ፡ ፍጹም አንድ ለመኾን በመቻላቸው ነው።

አለዚያ፡ ቀደም ብዬ እንደገለጽሁላችሁ፡ ያች፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሰውነቷ፡ ለእግዚአብሔር እናትነት የበቃች ከመኾኗ የተነሣ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር እም፡ ባልዋሓዳት ኖሮ፡ በእግዚአብሔር አብ አባትነትና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ምስጢራዊ ግብር፡ "ቃል ሥጋ ኮነ! ወኃደረ ላዕሌነ! ቃል ሥጋ ኾነ! በእኛም ዐደረ!" የተባለውን፡ እግዚአብሔር ቃልን፡ "በሰውነት ወለደችው!" ሊባል፡ እንዴት ይቻል ነበር? አዎን! ባልተቻለም ነበር።

በፀረ-እግዚአብሔርነቱ፡ ዋናው በዳይና ኃጢአተኛ፥ ሟችም የኾነውን ሰብአዊዉን ፍጡር ያካተተው፡ ሥጋዊውና ምድራዊው ፍጥረተ ዓለም፡-

- በመጀመሪያ የዳነው፡ እንዲህ፡ በእኔ፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ብቅዓት መኾኑን፥

- በመጨረሻም፡ በእባብና በዘንዶ የተመሰለው፥ "ሰይጣን"ም የተባለው፡ ያ ዲያብሎስ፡ ቀደም ብሎ፡ በመንፈሳዊው ፍጥረተ ዓለም፥ ኋላም፡ በሥጋዊው ፍጥረተ ዓለም ላይ፡ ከክፉዎቹ መሰሎቹ መናፍስትና ከሰብአውያኑ ተከታዮቹ ጋር በመተባበር፡ በይፋ የከፈተውን፡ ቋሚና ረዥም ጦርነት፡ ልጄ ወዳጄ፡ ኢየሱስ መሢሕ፡ በመስቀሉ ቤዛነት፡ በድል አድራጊነት ፈጽሞ በማስወገድ፡ አማናዊቷንና ዘለዓለማዊቷን የትንሣኤንና የሰንበትን ሰላም፡ ለሥጋዊውና ለምድራዊው ፍጥረተ ዓለም መልሶ በማቀዳጀቱ መኾኑን፡ በጥልቅ ልታውቁት፥ በአጽንዖትም ልታምኑበት ይገባል።

በቅዱሱ ኪዳን፡ ታማኞቹ ልጆቹ የኾኑት ኪዳናውያኑ ኢትዮጵያውያንና ኪዳናውያቱ ኢትዮጵያውያት፡ "ብኪ ድኅነ ዓለም! ወበወልድኪ ኮነ ሰላም! ፍጥረተ ዓለሙ ኹሉ፡ በአንቺ ዳነ! በልጅሽም፡ ሰላም ኾነ!" እያሉ፡ እስከዛሬ፥ ዛሬና ለወደፊትም፡ ለዘለዓለም፡ በዝማሬና በውዳሴ፥ በቅዳሴና በማኅሌት ሲያመሰግኑ ኖረዋል፤ እየኖሩ አሉ፤ ይኖራሉም።

ልታውቁት የሚገባችሁ፡ ሰባተኛው እውነታ፡ ይህ ነው።

## መፈጽም።

በድንግል ማርያም ሰውነት፡ "ኢትዮጵያ" ተብዬ፥ ታቦተ ጽዮንንም ኾኜ ስለተገለጥሁት፡ ስለእኔ፡ ስለእግዚአብሔር እም ማንነቴና ምንነቴ ዝክረ ነገር፡ የማታውቁ፥ እስካኹንም ያላወቃችሁ ካላችሁ፡ ከአኹን በኋላ፡ ታውቁት ዘንድ፡ የእውነታውን ማብራሪያ፡ እነሆ፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ ሰማችሁት!

እንግዲህ፡ ይህንኑ የሰማችሁትን የዐዋጅ ቃሌን፡ በተፈጥሮው ሥርዓታችን፡ በውስጣችሁ ባኖርናት፡ በእግዚአብሔርዋ እውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኳችሁ በተረጋገጠው፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ እምነታችሁ አጽንታችሁ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ ባላችሁ የልጅነትና የነጋሢነት፥ የካህንነትና የባለቤትነት፡ ሙሉ መብታችሁና ሥልጣናችሁ፥ ነጻነታችሁና ኃላፊነታችሁ፡ መልካሙን ገነታዊ ሕይወታችሁንና ቅን አገልግሎታችሁን፡ በያላችሁበትና በየተጠመዳችሁበት ሙያችሁ፡ በመታመን እንድትቀጥሉ ይኹን! እኛም፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ምንጊዜም ዐብረናችሁ ነንና፡ በሓሤት ደስ ይበላችሁ!

\+ + +

ተዐውደ፡ በግንቦት ፲፮ ቀን፥ ፳፻፯ ዓመተ ምሕረት ታወጀ።

ላእከ ኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር፣
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፣
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
ስመ ጥምቀቱ፡ ኂሩተ-ወልድ።